መ ቅ ድ ም

የየሃገሩ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባዎች /ሪፖርቶች/

የሰብአዊ መብት የየሃገሩ ሪፖርቶች (2006) በዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና በሠራተኛ ቢሮ የወጣ ማርች 6/2007 በዓለም ዙሪያ የተሻለ የግለሰብና የፖለቲካ ነፃነት እንዲሰፍን ሰዎች ጠንካራ ግፊት እያደረጉ ነው ። ለዴሞክራሲ ሰርዓት አራማጅ ተቋማት መኖርም ትግል እያደረጉ ነው ። ኘሬዚዳንት ቡሽ "ለድርድር የማይቀርቡ የሰው ልጆች የክብር ጥያቄዎች"ሲሉ የጠሯቸውን ጉዳዮች ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ ።

በራስ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችና ሊያጋጥሙ የሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢኖሩም አንዳንድ ብርቱ ግለሰቦችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ቡድኖች ሰብአዊ መብቶችን የሚፃረሩ ድርጊቶችን አጋልጠዋል። እነዚህ ወገኖች አናሣ የጐሣና ኃይማኖት ተከታዮችን መብቶች ያስጠብቃሉ ። እንዲሁም የሰራተኞችንና የሴቶችን መብቶች ከማስጠበቅ በተጨማሪ ለኤኮኖሚ ጥቅም ማግኛ ሲባል ሰዎችን የማዘዋወርን እኩይ ተግባር ለማስቆም ጥረት ያደርጋሉ ። ጠንካራና ቀልጣፋ የሲቪል ማኅበረሰብ ለመገንባት፣ ነፃና ትክክለኛ ምርጫዎች እንዲካሄዱ ለማድረግና ሕግን መሠረት ያደረገ ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ተጠያቂነት መኖሩ እንዲታወቅ ለማድረግ ይሰራሉ ። እነዚህ ለለውጥ የሚጓጉ አርበኞች የቀድሞውን ገደብ ሁሉ እየጣሱ በአዳዲስ ብይን እየለወጡት ይገኛሉ። በጥቂት ትውልዶች የሕልውና ዘመን በታደጊው ዓለም የነፃነት መንፈስ ተስፋፍቷል ። የኮሚኒስቶች አምባገነንነት ጐራ ተደረማምሷል፣ ብሎም አዳዲስ የዴሞክራሲ ጐራዎች ነፍስ ዘርተዋል።በአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ የተቀረፁት መብቶች፣ በየሃገራቱ ከበፊቱ የበለጠ የሕግ ከለላ አግኝተዋል።

ይህ ምስጉንና ድንቅ ሥራ ይቀጥላል። ቁርጠኛ ተቀናቃኞች ስላሉበት ሥራው ተጠናቆ ፍፃሜ አግኝቷል ማለት ግን አይቻልም ። የዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚያስፈራቸው ወገኖች የለውጥ ሐዋርያትን ቢቃወሙ አያስገርምም። ባለፈው ዓመት ውስጥ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችንና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አቀንቃኞችን መውጪያ መግቢያ ለማሣጣትና ለማስፈራራት ወይም የሚያራምዷቸውን ሥራዎች ለመገደብ ወይም ለማስቆም የተደረጉ ሙከራዎችን እይተናል ። ነፃ አመለካከት የሚያራምዱ ወገኖችን ለመቃወም ፍትሕ የማያሰፍኑ ሕጐች እንደ ፖለቲካ መሣሪያ እንዲያገለግሉ ተደርጓል ። ተቃዋሚ /ተቃራኒ/ ድምፆችን ዝም ለማሰኘት ሕጋዊ ያልሆኑ ዘዴዎችን ሥራ ላይ የማዋል ሙከራዎች አይተናል ።

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የጅምላ ጥቃት ሲደርስባቸው ነፃነትና ዴሞክራሲ ቀሰ በቀስ እየተዳከሙ ይሄዳሉ ። የዓለም ዴሞክራሲ ኃይሎች የሰብአዊ መብት፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጠበቆችን ጥበቃ ሊያደርጉላቸው ይገባል።ይህ ከወቅቱ ዲኘሎማሲያችን አቢይ ተልዕኮዎች አንደኛው ነው ። በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴራችን የወጡት የ2006 የየአገሩ ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሪፖርቶች በዚህ ረገድ የምናደርገውን ጥረት ወደፊት እንዲራመድ ይረዳሉ ። በነዚህ አሳቦች መደምደሚያነት እነሆ እነዚህን ሪፖርቶች *ለዶናይትድ ስቴትስ* ኮንግሬስ አቀርባለሁ ።

ኮንዶሊዛ ራይስ

የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር

መ ግ ቢ ያ :-

የሰብዓዊ መብቶች ትግበራን በተመለከተ የየሃገራቱ ዘገባዎች -2006 በዴሞክራሲ፤ ሰብአዊ መብቶችና ሠራተኞች ቢሮ የወጣ መግለጫ፣ ማርች 6/2006፤

መንግስታት ሀብአዊ መብቶችን በሥራ ለመተርጉም የገቡአቸውን ዓለምአቀፍ ግዴታዎች በምን ያህል አጥጋቢ ሁኔታ ለመፈፀም እንደቻሉ እነዚህ ዘገባዎች ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ በተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ የታቀፉ የሰው ልጅ መሠረታዊ መብቶች ጥያቄዎችን ኘሬዚደንት ቡሽ "ለድርድር የማይቀርቡ የሰው ልጆች የክብር መገለጫ ናቸው" ሲሉ የገለጧቸው ናቸው፡፡ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኮንዶሊዛ ራይስ እንዳሉት "እነዚህ ዓለም አቀፍ የሰባዊ መብት ድንጋጌዎች ባንድ ሌሊት ዕውን የሚሆኑ አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ ይዋሉ ይደሩ የሚባሉ ደግሞ አይደሉም፡፡"

እያንዳንዱ ግለሰብና በህብረተሰብ ውስጥ የሚንቀሳቀስ እያንዳንዱ ድርጅት የእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ተቀባይነትና ተፈፃሚነት እያደገ እንዲመጣ ባልተቋረጡ ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ የማሰከበሪያ እርምጃዎች አማካይነት ዓለም አቀፋዊ ዕውቅናቸውና ተከባሪነታቸው እንዲረጋገጥ ዓለማቀፋዊው ድንጋጌ ጥሪ ያደርጋል፡፡ ***የዩናትድ ስቴትስ መንግስት*** ሰብአዊ መብቶች ለማክበር የገባቸውን ግዴታዎች በጥብቅ ያከብራል፡፡ ይህን ሪፖርት የምንጽፈው ለአሸባሪዎች ጥቃት በተጋለጥንበትና ደህንነታችንን ለማስጠበቅ ስንል አፀፋዊ ርምጃ በመውሰድ ላይ በምንገኝበት ወቅትና ሰብአዊ መብቶች የማስከበር መልካም ስማችን ጥያቄ ውስጥ በገባበት ጊዜ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ***የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት*** በየጊዜው በሚያቀርባቸው ሪፖርቶች አማካይነት ሌሎች በእኛ ላይ ያላቸውን የሰብዓዊ መብት የማስከበር ጠንካራ እምነት እንዲጐለብት አበክረን እንሰራለን፡፡ ይህ ተግባራችን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች የፈረምናቸው ግዴታዎች አንድ አካል እንደሆነ አድርገን እንቆጥራለን፡፡ ተከታታይነት ያለው መሻሻል እንዲመጣ በቁርጥኝነት ለመሥራት ቃል ገብተናል፡፡ ***የዩናትድ ስቴትስ*** ሕጐች፤ ፖሊሲዎችና ተጠርጣሪ ሽብርተኞችን የማገት፤ በዕግት በሚቆዩበት ጊዜ ስለሚደረግላቸው አያያዝና ጉዳያቸው በፍርድቤት ስለሚታይበት ሁኔታ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ መሻሻል ተደርጓል፡፡ የመንግስታችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንከን የለሽ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ተጠያቂነት ግን አለበት፡፡ ጤናማውና ጠንካራው ሲቪል ማህበረሰባችን ፤ጉልበታሙ፣ ባለ ብዙ ሽፋኑና ትግርምት ፈጣሪው መገናኛ ብዙሀናችን፤ በነፃነት የሚሰሩት የመንግስታችን ዘርፎችና በጽኑ መሠረት ላይ የቆመው የሕግ ልእልና ስርዓታችን የማስተካከል ኃይል አላቸው ፡፡ እነዚህ ከዚህ በታች የቀረቡት የየሃገሩ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባዎች /ሪፖርቶች/ የኮንግሬሱ ውክልና ያላቸው ሲሆን በመላው ዓለም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ***የዩናትድ ስቴትስ*** መንግስት ከሚያደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ አንደኛው ተግባር ነው፡፡ እነዚህ ዓመታዊ ሪፖርቶች ለሶስት አሰርታት በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገራት በሰብአዊ መብቶች ረገድ በተገኙ ድሎችም ሆነ ገና ባልተከናወኑ ተግባራት ላይ በተደረጉ የግምገማ ጥናቶች ውስጥ እንደማጣቀሻ ሰነዶች እየተወሰዱ ሲሰራባቸው ቆይቶአል፡፡ መንግስታትና ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን እንዳይረገጡ፣ ብሎም ሃገሮች ሁሉ መሰረታዊ መብቶችን የማስከበር አቅማቸው እንዲጐለብት የድርጊት ትብብር መሰረት ሆነው አገልግለዋል፡፡

ሪፖርቶቹ በ2006 የነበሩትን የየሃገራቱን የሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ክንውን ይዳስሳሉ፡፡ እያንዳንዱ ሪፖርት ማጣቀሻ ሳያስፈልገው በራሱ ሙሉእ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በደምሳሳው የሚመሳሰሉ ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡

ከያንዳንዱ ሃገር በተወሰዱ ምሳሌዎች ማስረጃነት ቀጥለው ይቀርባሉ። የምናነሣቸው ምሳሌዎች አጠቃላይ ሁኔታውን ለማሣየት የተጠቀምንባቸው እንጂ ዝርዝር ስዕል የሚሰጡ አይደሉም።

ተሰፋ ሰጪ አዝማሚያዎችና፣

አሳሳቢ ዕውነታዎች፣

የነዚህ ሪፖርቶች አጠቃላይ ግምገማ እንደሚያሳየው በመላው አለም ሰዎች በ2006 ለመብቶቻቸው መከበር ሲሉ መንግስታት ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ፣ ትክክለኛ ሕጐች እንዲደነገጉ፣ ስለፍትህ መስፈን የሚያስሙት ድምጽ እንዲሰማና በምርጫ ጊዜ የሚሰጡት ድምፅ ተገቢ ዋጋ እንዲሰጠው አበክረው ታግለዋል። የዜጐች የክብር፣ የነፃነትና የእኩልነት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት የሚችሉት ዴሞክራሲያዊ ሰርአት ያለው መንግስት ሲኖር ብቻ መሆኑን የመረዳት ጉዳይ በሰዎች ዘንድ እያደገ መጥቶአል። እነዚህ አዝማሚያዎች በእውነትም ተስፋ ሰጭ ክስተቶች ናቸው። ይሁን እንጂ ሪፖርቶቹ አሳሳቢ እውነታዎችንም ያንፀባርቃሉ።

መጀመሪያ በሰብአዊ መብቶች መከበርና በዲሞክራሲ ስርዓት መስፈን እረገድ የተገኙ ድሎች እልህ አስጨራሽ የነበሩ ሲሆን ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረጉ ሥራም የዚያኑ ያህል የማያቋርጥ ትግል የሚጠይቅ ነው። ጥቂት ሃገሮች ከግምት ውስጥ የሚገባ እርምጃ ሲያሳዩ፣ ጥቂቶች ደግሞ ወደ ኋላ ቀርተዋል። ሌሎች ደግሞ ጭራሽ (እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ) የኋሊት ሄደዋል።

ከዚህ በታች የተጠቀሱ በርካታ ምሳሌዎች እንደሚያመለክቱት፡ የየሃገሩ የሰብአዊ መብት ሪኮርዶች በጅጉ የተለያዩ ናቸው። ልዩነቶቹም የሚወስኑት፡ መንግሥታት ለሰብአዊ መብቶች ባላቸው የቁርጠኝነት መጠን፣ በተቋማዊ አቅም፣ የሙስና ተግባራት ጥልቀትና ስፋት እንዲሁም በሲቪል ማህበረሰቡ ጥንካሬና በመሳሰሉት ታሳቢዎች ነው።

ጃነወሪ 2006 *በላይቤሪያ* በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የተመረጠው ***የላይቤሪያው*** ሕብረት ፓርቲ መንግስት የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዚዳንት በሆኑት በኤለን ጆንሰን ሰርሊፍ የሚመራ የመጀመሪው የአፍሪካ ሃገር ነው። ይህ አዲስ መንግስት፣ ከ2003 ጀምሮ ለ14 ዓመት ጥፋት ያስከተለውን ጦርነት አስወግዶ በሽግግር መንግስትነት ላይቤሪያን ሲያስተዳድር የነበረውን መንግስት የተካ ነው ። አዲሱ የኤለን ጆንሰን መንግስት ያለፉ የሰብአዊ መብት ጉድለቶችን ለማረም ከግምት ውስጥ የሚገቡ የማሻሻያ እርምጃዎችን ወስዶአል። የእርምት እርምጃዎችን ሲወስድ የሃገሪቷን የፍትህ ዘርፍ መልሶ ሲያቋቁምና የሕዝብ መብት ተከራካሪ ቢሮ በዋና ከተማው ሲመሰረት የአለም አቀፍ አጋሮችን ድጋፍ አግኝቶአል።

ፕሬዚዳንቷ በሙስና የባለጉ በርካታ የመንግስት ባለስልጣናትን ከሥራ አሰናብተዋል ወይም ደግሞ አግደዋል። በ2005 የተቋቋመው የሃቅና የእርቅ ኮሚሽን በጦርነቱ ወቅት የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችንና የጦር ወንጀሎችን ለመመርመር የዓይን ምስክሮችን መስማት ጀምሯል። ከዚህ አመርቂ እርምጃ በተቃራኒው *ላይቤሪያ* የሰብአዊ መብት አጠባበቅ ፈተናዎች ዛሬም አለበት። እነዚህም ደካማውን የፍትህ ሥርአት፣ ቅጣት የማይነካው የባለስልጣናት ሙስና፣ ጾታን መሰረት ያደረገ ኢፍትሃዊነት፣ ወደ ሕዛናት ጉልበት ብዝበዛ የሚወስድ ማቆሚያ ያጣ ድህነት መኖር፣ ለላይቤርያ መንግስት ፈታኝ ጉዳይ ሆኖአል።

የፖለቲካ እንቅስቃሴ ይበዛባቸው በነበሩ *የኤንዶኔዝያ* ክፍለ ግዛቶች በጦር ኃይሎችና በፖሊስ ሰራዊት ይፈጸሙ የነበሩ ግድያዎች በዓመቱ ውስጥ በእጅጉ ቀንሰዋል ። በክፍለ ሃገራት በሞግዚት ግዛቶች፤ ወረዳዎችና በራስ ገዝ ከተሞች ደረጃ ነፃና ፍትሐዊ የሆኑ 54 ጠቅላላ ምርጫዎች ተካሄደዋል። ይበልጥ ደግሞ በታህሳስ ወር *በአሴህ* ግዛት የአስተዳደሩን ሥልጣን ለመያዝ በተካሄደው ውድድር የአማፂዎች መሪ ያሸነፉበት ምርጫ የሚጠቀስ ነው። ሐይማኖትን መሰረት ያደረገ እና በማህበረሰቦች መካከል የነበረው ብጥብጥ ባጠቃላይ የበረደ ቢሆንም በአንዳንድ ቦታዎች እንደቀጠለ ነው ። በኢንዶኔዚያና በምሥራቅ ቲሞር በስልጣን ላይ ያሉ መስተዳድሮችና ፍ/ቤቶች ቀደም ሲል የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን መርምረው ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኙ ለማድረግ አልቻሉም።

ምንም እንኳን አሁንም ችግሮች መሉ በመሉ ያልተቀረፉ ቢሆንም *የምሮክ* የሰብአዊ መብት ሬኮርድ የጐላ መሻሻል አሣይቷል። መንግስት ለቀድሞ የሰብአዊ መብት ጥሰት ትኩረት ለመስጠት ሲል በሰብአዊ መብቶች አማካሪ ምክር ቤት አማካይነት አግባብነት ላልነበራቸው እስራቶች፤ የደረሱበት ላልታወቀ ግለሰብ ጉዳዮችና ከ1956 እስከ 1999 የሥልጣን ብልግና ለተፈፀመባቸው ካሣ እንዲያገኙ በማደረግ ችግሮቹን ለመፍታት ሞክሯል።

መንግስት በመጋቢት ወር ማሰቃየትን የሚገታ ሕግ አወጣ። ይሁን እንጅ በፀጥታ ኃይሎች የሚፈፀመው ሰዎችን የማሰቃየት ተግባር አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን ሪፖርቶች ያመለክታሉ። በኘሬስና በንግግር ነፃነቶች ላይ የተጣሉ ገደቦች ቢኖሩም በኘሬስ ሕትመቶች ላይ ግልፅ የሆኑና ሰፋ ያሉ የሕዝብ ክርክሮች ተደርገውባቸዋል ። ባመቱ ውስጥ መንግስት የተገደበ የንግግር ነፃነት የጣሱ በርካታ ጋዜጠኞችን ስለቀጣ ብዙዎቹ ራሣቸውን ሴንሰር እንዲያደርጉ ተገደዋል። ለወሲብና ለሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ሰዎችን የሚያዘዋውሩ ግለሰቦች ጉዳይ አሣሣቢ እንደሆኑ ቀጠሉ እንጅ አንዳችም ርምጃ አልተወሰደባቸውም። መንግስትና ሲቪል ማህረሰቡ ሰዎች ማዘዋወርን በተመለከተ የተሻለ ንቁ ተሳትፎ አድርጓል።

ዴሞክራቲክ ሬፐብሊክ ኮንጐ ከ45 ዓመታት በኋላ የመጀመሪያውን ዴመክራሲያዊ የኘሬዚዳንትና የሕግ አውጪዎች ምርጫ አካሂዷል። በዚህ ምርጫ ለሶስት ዓመት የቆየው የድህረ ጦርነት የሽግግር አስተዳደር ሊያበቃ ችሏል። በምትኩም አዲስ ሕገመንግስት በሥራ ላይ ውሏል።ይሁን እንጅ የሰብአዊ መብት አከባበር ሁኔታ ከበፊቱ የተሻለ አይደለም። እየቀነሰ የመጣ ከሚመስለው ግጭት አንፃር የመንግስት የቁጥጥር ኃይል አሁንም ደካማ ነው። የታጠቁ ቡድኖች የጭካኔ ተግባራት ይፈጽማሉ፤ የመንግስት የደህንነት ኃይሎችም በማናለብኝነት የግፍ ሥራ ይሰራሉ ። ስለሆነም በመላው ኮንጐና በምሥራቁ ግዛት የሰብአዊ መብቶች ተከብረዋል ለማለት አይቻልም ።

በሄይቲም በ2006 ዜጐች ለሰብአዊ መብቶች መከበር ያላቸውን ቁርጠኝነት ለማሣየት ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ሶስት ጊዜ በሰልፍ ወጥተዋል። ከ3.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጐች የኘሬዚዳንት ምርጫ ለማድረግ ተመዝግበዋል። ከተመዘገቡት 70% የሚሆኑ መራጮች የካቲት ላይ በነበረው የመጀመሪያው ዙር የፕሬዚዳንትና የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫዎች ተሳትፈዋል። አንፃራዊ መረጋጋት የነበረውና ከብጥብጥ ነፃ የሆነ የምርጫ ሂደት ከተከናወነ በኋላ መራጮች ለፕሬዚዳንት ሬኔ ፕሪቫል ድምፅ ሰጡ፤ 129 የፓርላማ መቀመጫዎችን የሚይዙ ተመራጮችንም መረጡ።

ሄይቲአውያን ባስር ዓመት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በታህሳስ ወር የከተማ አስተዳደር ምርጫዎችን አካሄዱ። ሙሉ በሙሉ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን ገና መሠራት ያለባቸው በርካታ ሥራዎች አሉ። በዚህ ረገድ በወጉ የማይሰራው የፍትህ ሥርዓት የተሃድሶ ሥራ ይፈልጋል። የሃገሪቷን ብሔራዊ ፖሊሲም እንደገና ማደራጀትና ባለፈ የተሳሳተ አሠራር ላይ እርምት ማድረግ ያስፈልጋል።

በኡክሬይን ከግምት የሚገባ የሰብአዊ መብቶች መከበር ከድህረ ብርቱካናማ አብዮት ወዲህ መሻሻል ተደርጓል። በመጋቢት ወር 2006 የተካሄዱት ምርጫዎች ከ15 የነፃነት ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ በነፃነት ሥሜት የተካሄዱ ነበሩ። ሀገሪቷ በፕሬስ፣ በመደራጀት ነፃነትና በሲቪል ማህበረሰብ እድገት ረገድ መሻሻሏን ቀጥላለች። ከነዚህ መሻሻሎች በተቃራኒ በልዩ ልዩ የመንግስት አስተዳደር ዘርፎች ሙስና ገና አሁንም የተንሠራፋ ከመሆኑም በላይ በርካታ ችግሮች አልተፈቱም።

በ2005 በተደረገው ዴሞክራሲያዊ የአስተዳዳሪዎች ምርጫ *የኪርጊዝታን* የሰብአዊ መብቶች ሬኮርድ በከፍተኛ ሁኔታ ቢሻሻልም በ2006 ለአንድ ሳምንት የተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ደግሞ ጥድፊያ በሰፈነበት ሁኔታ ሕገመንግስቱን አሻሽለውታል። የተሻሻለው ሕገመንግስት በመንግስት የተለያዩ ዘርፎች ላይ ሚዛናዊ የሆነ አሠራር እንዲሰፍንና ቁጥጥር እንዲደረግ የሚያስችል ሥርዓት ፈጠረ። ይሁን እንጅ በታህሳሥ መጨረሻ ላይ እነዚህን ቁልፍና ሚዛናዊ የሆኑ የቁጥጥር ሥርአቶች የሚሸር ሌላ ሕገመንግስት ፓርላማው አፀደቀ። መንግስትም ከውጪ በሚገኝ ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶችን ቁም ስቅል ያሣያቸው ጀመር።

ፕሬዚዳንት ሙሻራፍ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እንደሚያደርጉና በብልህነትና ሀቀኝነት የተደገፈ አመራር ሥራ ላይ እንደሚያውሉ ቃል ቢገቡም *ፓኪስታን* የሰብአዊ መብት ሬከርድ አሁንም ደካማ ነው። ከቦታ ቦታ የመዘዋወር፣ የንግግር፣ በማህበር የመደራጀትና የሃይማኖት ነፃነት ገደቦች ዛሬም አልተነሱም።

በየክፍለሀገሩ ያሉ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና የተቃዋሚ ፖለቲከኞች የት እንደደረሱ ያለመታወቅ ጉዳይ እንደቀጠለ ነው። የዚህ ዓይነቱ ተግባር የሚፈፀመው በተለይ የውስጥ ብጥብጥና አመጽ በሚዘወተርባቸው የሃገሪቱ ክፍሎች ነው። የፀጥታ ኃይሎች የፍርድ ሂደት ያላፀደቃቸው ግድያዎች ይፈጽማሉ። ያለፍርድ ቤት ትዛዝ ማሰርና ማሰቃየት የተለመዱ ተግብራት ናቸው። መንግስትና የፖሊስ ሀይሉ ሙስና የፅለት ተለት ተግባራቸው ነው። አዎንታዊ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል የተለየ ተግባር በታህሳስ ወር ብሔራዊ ጉባኤው ያሣለፈውና ፕሬዚዳንት ሙሻራፍም በፊርማቸው ያፀደቁት ለሴቶች ጥበቃ እንዲደረግ የወጣው ሕግ ነው። ይህ ሕግ አንድ የፓኪስታን መንግስት በሠላሣ ዓመት ውስጥ የሴቶችን መብት የሚረግጡ ሕጐችን ያስቆመበት የመጀመሪያ ርምጃ ነው።

ይህ ሕግ የወሲብ ጥቃትን በሸሪአ ሕግ ከመዳኘት ይልቅ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንዲታይ የሚያደርግ። በ1979 የወጣውን አስገድዶ የመድፈርና የማመንዘር ወንጀል በሀገሩ መሪ አካል ወጥቶ የነበረውን የሁዱድ ልቅ የወሲብ ተግባር ማስቆሚያውን ትዕዛዝ አሻሻለው። ይህ አዲስ ሕግ የተደፈሩ ሴቶች ክስ ለመመሥረት አራት የወንድ ምሥክሮች ማቅረብ መቻል አለባቸው የሚለውን ግዴታ አስወገደው።

ምንም እንኳ *ግብፅ* በ2005 ለመጀመሪያ ጊዜ የመድብለ ፓርቲ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በማድረግ የዴሞክራሲ ብልጭታ ብታሣይም በ2006 ለበለጠ ዴሞክራሲያዊነትና ተጠያቂነት የተደረገው ህዝባዊ ጥሪ ከመንግስት በኩል ጠንካራ ተቃውሞ ገጥሞታል። የቀድሞ ፕሬዚዳንታዊ እጩ የነበሩት የአይማን ኑር የተደጋገመ አስራት በሀገሪቷ እየተካሄደ ነው በሚባለው የፖለቲካ ተሃድሶና ዴሞክራሲ ላይ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ፈጥሯል። በ2005 የተጀመረውን አዝማሚያ በመቀጠል የግብፅ መንግስት በመቶዎች የሚቆጠሩ የለውጥ አራማጆችንና የተከለከለውን ነገር ግን በትዕግስት የተያዘውን የእስልምና ወንድማማችነት አባላትን እየያዘ ለብዙ ሣምንታት ያሥራል። በየካቲት ወር ከተጽእኖ ነጻ የሆነ የዳኝነት ሥራ እንዲኖር በመጠየቅ ግልጽና ይፋ ጥሪ በማደረጋቸው ሁለት ዳኞች ለጥያቄ ቀርበው ነበር። የግብፅ ፖሊስ ኃይል የዳኝነት ነፃነትን ለመደገፍ በተጠራ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተካፈሉ 500 ታጋይ ግለሰቦችን ይዞ አስሯል። ከዚህ በተጨማሪ በባለሥልጣናት የተፈፀሙ አሰቃቂ የማሰቃየት ተግባራት በውል ተመዝግበዋል። መንግሥት በርካታ የድረገጽ መረጃ አሰራጮችን ይዞ አሥሯል፣ አግቷል፣ አንገላቷል።

የካዛክስታን መንግስት አስቸጋሪ የምዝገባ መሰናክሎችን በሥራ ላይ በማዋል ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባን በማወክና በመከልከልም ጭምር የፖለቲካ ተቀዋሚዎቹን እንቅስቃሴዎች ገድቧል። አማራጭ ሃሳቦችን ለማቅረብም ሆነ ለተሃድሶ መቆም እንዳይቻል የመንግስት ደጋፊ ፓርቲዎችን በማዋሃድ እና የአታን ፓርቲያቸውን መሪነት በማጠናከር ፕሬዚዳንት ናዛርባዬቭ በሃገራቸው ጠባብ የሆነ የፖለቲካ መንቀሳቀሻ ድባብ ፈጥረዋል። የፖለቲካ መንፈስ ያላቸውና በመሰብሰብ ነፃነት ላይ የተነጣጠሩ ክሶችን በመመሥረትና ገደቦችን በመጣል የፕሬስ ነፃነትን የሚያሽመደምዱና መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶችን ቁምስቅል የሚያሣዩ ሕጐችን መንግስት አውጥቷል።

የሩሲያ መንግስት ኃይልን የተማከለ ለማድረግ የሕግ አስፈፃሚው ዘርፍ ጥንካሬ እንዲያገኝ የማድረግ ጥረቱን ቀጥሎበታል። በዚህ ረገድ የምርጫ ሕጐች እንዲሻሻሉመደመዱ ፓርቲዎችን የሚመለከቱ አዳዲስ ሕጐች እንዲደነገጉ በማድረግ፣ የፓርቲዎችን እንንስቃሴዎች በተፈቀደላቸው መንገድ ብቻ እንዲሄዱ አድርጓል። የተከሰተ ችግር ቢኖር ችግሩን ለማጣራትና ተግባራቸውን ለመገደብ እስከ ማገድ ድረስ የሚያስችሉና ለመንግስት ሰፊ ኃይል ፈቃድ ያጐናፀፉ ሕጐች ወጥተዋል። ከአቤቱታ ሰሚ የመንግስት ምክር ቤት ጋር አብሮ በመሆን ለሙስናና ለሕግ አስፈፃሚነት አድሎአዊ መረጣ፣ በሕግ ተርጓሚው ላይ የሚደረግ የፖለቲካ ጫናና መንግስታዊ ባልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶችና በብዙሃን መገናኛዎች ላይ የሚጣሉ ገደቦች የመንግስትን ተጠያቂነት ይብሱኑ እየሸረሸሩት ሄዱ። *በቾችንያና* በሌሎች የሰሜን *ኮከሱስ* ግዛቶች የባሰባቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አሁንም እንደቀጠሉ ነው። ከሚጠቀሱት ውስጥ ህግ ያላፀደቀው ግድያና *የቼችንያ* ዜጐችን ማንቋሸሽ፣ ማዋከብና ልዩ ልዩ ስሞች እየሰጡ ማዋረድ የፌዴራልና *የቼችንያ ሪፐብሊክ* የጥበቃ ኃይሎች ከሚፈጽሟቸው ተግባራት ጥቂቶቹ ናቸው። አማኒ ተዋጊዎች *በቼችን* ክልል ውስጥ የሽብር ፍንዳታዎችን አፈንድተዋል። በተጨማሪም ፖለቲካዊ ሽፋን የተሰጣቸው ሰዎችን የመሰወር ተግባራት ፈጽመዋል። የአውሮፓው የሰብአዊ መብት ፍርድ ቤት ለነዚህ ሁሉ ጥሰቶች *ሩሲያን* ተጠያቂ አድርጓታል።

በቬኔዙዌላ የሻቬዝ መንግስት ኃይሉን የተማከለ በማድረግ የሕግ አስፈፃሚውን ዘርፍ ማጠናከሩን ቀጥሎበታል። ተቀዋሚ ወገኑንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እያዋሰደ እና ስርአቱንም ነፃነቱን በማሳጣት እያደከመው ይገኛል። ሻቬዝ ከመቶ 63 የድምፅ ብልጫ በማግኘት ያሸነፉበትን የታህሳሱን ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ አለምአቀፍ ታዛቢዎች ነፃና ትክክለኛ ሲሉ ገልፀውታል። ከምርጫው በኋላ ለብሔራዊው ምክር ቤት ባደረጉት የመክፈቻ

ንግግር፣ ፕሬዚዳንት ሻቬዝ ተቀዋሚዎቻቸው አንድም መቀመጫ ያላሸነፉበትን ምክር ቤት አባላትን በአዋጅ እንዲያስተዳድሩ ሥልጣን እንዲሰጡአቸው ጠይቀዋል።

በፊጂና በታይላንድ ወታደራዊ ኃይሎች በዴሞክራሲ የተመረጡ መንግስታትን በመፈንቅለ መንግስት አስወግደዋል።

በሁለተኛ ደረጃ አዘውትሮ እየታየ ያለው አሣሣቢ ዕውነታ የውስጥ ወይም ድንበር ዘለል ግጭት እየተከሰተ ደህንነትን ማወኩ ወይም የሰብአዊ መብቶችን እያጠበበና ዴሞክራሲያዊ መንግስት እንዳይኖር የሚፈጥረው እንቅፋት ነው።

ምንም እንኳን *የኢራቅ መንግስት* ብሔራዊ እርቅን፣ ሀገርን እንደገና የመገንባትና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ቁርጠኝነት እያሣየ ቢሆንም በ20006 ሥር እየሰደደ የሚገኝ ወገን የለየ ብጥብጠና የሽብር ተግባር የዴሞክራሲ መሻሻልን በጅጉ እየጐዳ በመጣ ሁኔታ እየተቸገረ ነው። ምንም እንኳን የኢራቅ ሕገመንግስትና ሕግ የሰብአዊ መብቶችን የማስከበሪያ ኃይል እንዲኖራቸው የተቀረፁ ቢሆኑም ሰብአዊ መብቶችን ከሁለት አግጣጫ እየወጉ ናቸው። አንደኛው ወገን በመንግስት ላይ ግልጽ ተቃውሞ ያወጀው *የአልቃኢዳ ሽብርተኞችና* ሌሎች እርቅ የማይሹ *የባአዝ* ፓርቲ አባላት ቅሪቶችን ያቀፈ ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የሽምቅ ውጊያ የሚያካሄዱ ተቃዋሚ ኃይሎች፣ *የሺአ ማሊሻያ* አባላትና ለመንግስት የስም ብቻ ትብብር የሚያሣዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤት የደህንት ኃይል ሰዎች ያሉበትና የማሰቃየት ፀያፍ ሥራ እየሰሩ ያሉ የሚገኙበት ነው ።

በ2001 ታሊባን ከሥልጣን ከተወገደ ወዲህ *ሉፍጋኒስታን* በሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ረገድ የማይናቅ መሻሻል ብታደርግም የሰብአዊ መብት ሪኮርዷ አሁንም የሚያስመካ አይደለም። ይህ የሆነበት ምክንያት ከማንም ይበልጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ደካማነትና ድንጋይ ነክሰው የሚዋጉ አማጽያን የሚያደርሱት እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ ነው። የታሊባን ተዋጊዎች አልቃኢዳና ሌሎች ጽንፈኛ ቡድኖች በመንግስት ባለሥልጣናት፣ በጥበቃ ኃይሎች፣ መንግስታዊ ባልሆኑ

ድርጅቶችና ሌሎች የርዳታ ደርጅት ሠራተኞች ላይ የሚያካሂዷቸውን የጥቃት ተግባራት እያጠናከሩ መጥተዋል። በ2006 የአጥፍቶ መጥፋት የቦንብ ፍንዳታዎች በጅጉ ጨምረዋል። በትምህርት ቤቶችና በመምህራን ላይ የሚፈፀመው ጥቃት ያንኑ ያህል ጨምሯል። በማንአለብኝነት የሚደረጉ ሰዎችን የማገት፣ በሥር የማቆየት፣ ያለ ፍርድ መግደል፣ ማሰቃየትና አስከፊ የሆኑ የእሥር ቤት አያያዝ ሁኔታ ሪፖርቶች መውጣት እንደቀጠሉ ነው። ፕሬዚዳንት ካርዛይ በታህሣስ ወር ቀድሞ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ረገጣዎችን እንደገና በመመርመር የፍትህ መስሪያ ቤቶችን አቅም ለማጐልበት የሽግግር ጊዜ የፍትህ ማስፈን ፕላን አውጥተዋል።

ከ2005 አስቀድሞ ፕሬዚዳንት ከነበሩት ከራፊቅ ካሪሪ ግድያ በኋላና ለሦስት አሠርት አመታት ሀገሪቷን ይዘው የነበሩት የሶሪያ ወታደሮች ለቀው ከወጡ ወዲህ *በሊባኖስ* የተወሰዱ የማሻሻል ርምጃዎች ተስፋ ሰጪ ነበሩ። ነገር ግን በሐምሌና ነሐሴ 2006 በሒዝቦላና በእስራኤል የጦር ኃይሎች ግጭት የተነሳ የመሻሻል ተግባራቱ ተስተጓጉለዋል። ከግጭቱ በፊት የሊባኖስ መንግስት ብዙዎቹን የፖለቲካ ማህበራትና ፓርቲዎችን ሲያውኩ የነበሩ እንቅፋቶችን ማስወገድ ጀምሮ ነበር። ይሁን እንጅ ሂዝቦላ ከሊባኖስ የእስራኤልን ድንበር ዘሎ ገብቶ

በርካታ የእስራኤል ወታደሮችን ከገደለና ካገተ በኋላ የእስራኤል ጦር ኃይሎች የሊባኖስን ድንበር አቋርጠው በመግባት ምላሽ ሰጡ። በተባበሩት መንግስታት አማካይነት በተደረሰው የተኩስ ማቆም ስምምነት የተነሣ ግጭቱ ሊቆም ችሏል። *የሊባኖስ* ጥበቃ ኃይሎችና የተባበሩት መንግስታት ሕግ አስከባሪ ኃይሎች በደቡብ ሊባኖስ ቢሰፍሩም የሊባኖስ ሚሊሺያዎችና ሒዝቦላ በሰፋፊ የሊባኖስ ግዛቶች ውስጥ የሚኖረውን ሕዝብ ድጋፍ ስላገኙ የተኩስ ማቆም ስምምነቱ ፀንቶ እንዳይቆይ እያደረጉ ነው።

በምስራቅ *ቲሞር* በብሔራዊ መከላከያ ኃይሉና ከጦር ኃይሉና ከፖሊስ ሠራዊት በከዱና ከሲቪል ኃይሎች በተውጣጡ ወገኖች መካከል ጠንካራና ተከታታይ ግጭቶች ተደርገዋል። እነዚህ ግጭቶች በዋና ከተማው ለሕግ ተገዥ ያልሆኑ ጋጠወጥ ቡድኖችና ወሮበሎች የሚቀሰቀሰው ብጥብጥ መነሻ ሆኗል። በመንግስት ጥያቄ የመጡ *የአውስትራሊያ*፣ የኒውዚላንድ፣ የማሌዢያና የፖርቱጋል ወታደሮች ኃላፊነት ወስደው የከተማውን ደህንነት እየተቆጣጠሩ ነው። በነሐሴ 25 የምስራቅ ቲሞር ጥምር ተልዕኮ የተባለው የተባበሩት መንግስታት ሃይል የከተማዋን ፖሊሳዊ ጥበቃ ኃላፊነት ተረክቦ እየሰራ ነው። ይህ የውስጥ ብጥብጥ በግምት 150,000 የሚደርስ ህዝብን አፈናቅሏል። ይህ ማለት ከጠቅላላው የሀገሪቷ ሕዝብ ብዛት 15 በመቶው ተፈናቅሏል ማለት ነው።

ሦስተኛ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ከተገኙት የሰብአዊ መብቶች መከበርና የዴሞክራሲያዊ መርሆች መስፈን ድሎች በተቃራኒ የሰው ልጅ የነፃነት ሕልም ቢያልምም ዛሬም ገና በፍርሃት ተውጦ ይገኛል።

የመንግስት ሥልጣን ምንም ዓይነት ተጠያቂነት በሌለባቸው ገዥዎች እጅ ውስጥ በተከማቸባቸው አገሮች እነዚህ ገዥዎች ስማቸው ፈላጭ ቆራጭ ይሁን ወይም አምባገነን መንግስት በዓለም ላይ የሰብአዊ መብት ረጋጭ ስርዓቶች እንደሆኑ ቀጥለዋል።

በ2006 *የሰሜን ኮሪያ* መንግስት ከዓለም ማህበረሰብ የተገለለና የሰብአዊ መብት ረገጣ የነገሠበት ብቸኛ መንግስት ስባረ። በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት የዜጐችን የመናገር፣ የፕሬስ፣ የመሰብሰብና በማህበር የመደራጀት ነፃነቶችን በቁጥጥሩ ሥር በማዋልና ከቦታ ቦታ የመዘዋወርና ሠርቶ የማደር መብቶችን የመገደብ ከፍተኛ ተግባር ያከናውናል። የሀገሩ ሕገመንግስት የዕምነት ነፃነትን ይፈቅዳል። ይሁን እንጅ እውነተኛ ነፃነት የለም። ከ150,000 እስከ 200,000 የሚገመት ሕዝብ፣ የፖለቲካ አስረኞችን ጨምሮ በስር ማቆያ ካምፖች የታጐረና በርካታ እሰረኞች በመሰቃየታቸው፣ በመራባቸው፣ ለበሽታና ለብዙ ችግሮች በመጋለጣቸው የተነሣ ሞተዋል።

የበርማ ወታደራዊ መንግስት በስልጣን ለመቆየት ግድያዎችን፣ አስገድዶ መድፈርን፣ ማሰቃየትን፣ በምክንያት ያልተደገፈ እስራት ማካሄድን፣ በተለይ ደግሞ አናሣ ጐሣዎችን ከኖሩበት ሥፍራ በግዴታ እያስነሱ የማስፈርን ዘዴ በሠፊው ተጠቅሟል። እስረኞችና በማቆያ ቤት ያሉ ግለሰቦች ለኢሰብአዊ ድርጊቶች እንዲጋለጡ አድርጓል። በፖለቲካ ግንባር ቀደም መሪዎች ላይ ሥለላ የማካሄድ፣ መውጫ መግቢያ የማሳጣትና የማሰር ተግባሩን ቀጥሎበታል። የኖቤል ተሸላሚዋንና የተቃዋሚ ፓርቲውን መሪ ሣን ሱ ኪን በቁም እስረኛነት ከቤታቸው እንዳይወጡና ከሰው እንዳይገናኙ አድርጓል። አንድ ሺ አንድ መቶ የሚሆኑ የፖለቲካ እስረኞች በሥር ቤት በመንገላታት ላይ ይገኛሉ። በግዳጅ የጉልበት ሥራ የማሰራት፣ ሰዎችን ከቦታ ቦታ የማዘዋወር፣ ሕፃናትን ለውትድርና የመመልመልና የሃይማኖት መድሎ ተስፋፍተዋል። መንግሥት በማስመሰል የተሸፈነ የፓርቲዎች ብሔራዊ ስብሰባ ጥሪ አድርጓል። የስብሰባው ተካፋዮች በመንግስት ተለይተው የተጠሩና አንዳችም ክርክር ማንሳት የማይችሉ ነበሩ። አገሪቱን ወደ ዴሞክራሲ ጎዳና እንደሚያስገባት ተቆጥሮ የተጠራው ብሔራዊ ሰብሰባ

የ1990ውን ምርጫ ዋጋ ለማሠጣት የተነደፈ ዘዴ ነበር። ዋና ዓላማውም አዲስ ሕግ ለመቅረጽና አፈቃራ-መንግስት የሆነ ሕገመንግስት ለማጽደቅ ነበር። የመንግስቱ ጭካኔና የጥፋት አስተዳደር ዜጎች እንዲሰደዱ፣ የተላላፊ በሽታዎችን መስፋፋት፣ አደንዛዥ እፆችንና ሰዎችን ወደ ጐረቤት ሀገሮች የማሻገር ተግባራት እንዲስፋፋ አድርጓል።

የኢራን መንግስት የመናገርና የመሰብሰብ ነፃነትን አይኑን ጨፍኖ (አለሃፍረት) እየጣሰ ነው። አሻፈረኝ ባዮችን፣ ጋዜጠኞችንና የለውጥ አራማጆችን ከተግባራቸው ለመግታት የሚያስችለው ሥራውን እያጠናከረ ነው። ይህም፣ ምክንያት የማይጠየቅበት በሥር የማጋዝና በሥር ቤት የማቆየት፣ በሥር ቤት ውስጥ ልዩ ልዩ የማሰቃያ ተግባራት የመፈፀም፣ የሰዎችን ደብዛ የማጥፋት፣ ከመጠን ያለፈ ኃይል የመጠቀምና በትክክለኛ መንገድ በሕዝብ ፊት የመዳኘት ዕድል ማጣጣትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። የብሃይና የሌሎች አናሣ ሀይማኖት ተከታዮችን ማሰርና በግለሰቦች ላይ ችግር በሰፊው ማድረስ የተለመደ ሥራው አድርጐታል።

የኢራን መንግስት እስራኤላውያን በሂትለርና በናዚ ፓርቲ መሰቃየታቸውን የሚያስተባብል በከፍተኛ ደረጃ የተወገዘ ጉባኤ አካሄደ። ወደ ታህሣሥ 15ቱ ስብሰባ መዳረሻ በነበረው በምርጫ ኤክስፐርቶች ስብሰባ ለመመረጥ የፈለጉና ከሁለት ሦስተኛ በላይ ቁጥር የነበራቸው ወንድና ሴት አመልካቾች እንዳይወዳደሩ በመደረጋቸው ብዙ መቀመጫዎች ባዶአቸውን ቀርተዋል። በመቶ የሚቆጠሩ ለከተማ አስተዳደር ምርጫ የውድድር አመልካቾች ተገቢ አይደላችሁም ተባሉ። የኢራን መንግስት በ2006 የአገር ውስጥም ሆነ የአለምአቀፍ ሕብረተሰብ ሕገወጥ አሰራሩን እንዲያቆም ጥሪ ቢያደርጉለትም *በሶሪያና በሊባኖስ* የሚካሄዱ የሽብር ንቅናቄዎችን በመደገፍ ጭራሽ የገዘፈን ጀሮ ይሰጠኝ አለ። እንዲያውም የተባበሩት መንግስታት አባል የሆነችውን አገር ሊባኖስን ለማጥፋት ጥሪ አድርጓል።

በዚምባቡዌ የሙጋቤ መንግስት ሀገሩን ሙሉ ያዳረሰ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዲስፋፋ አድርጓል።

ይፋ የሆነ የሙስና ተግባርና ማናለብኝነት በጅጉ ተስፋፍተው ነበር ። የ2002ቱ የመንግስት ምስጢሮች ሕግና የሥርዓትና የደህንነት ሕግ በሥራ ላይ እንዲቆዩ ተደርገዋል። በመሆኑም የሲቪል ነፃነቶችን በማያላውስ ሁኔታ ገድበው ነበር። በ2006ቱ የማሙያ ምርጫዎችና የገጠር ወረዳ ምክር ቤት ምረጫዎችን መንግስት ጣልቃ እየገባ ስላደናቀፋቸው መራጮች ለተወካዮቻቸው ድምፅ ሊሰጡ አልቻሉም። ይህ በምርጫ ሂደት ውስጥ ጣልቃ እየገቡ የማወኩ ነገር ምርጫዎቹ ወደ ገዥ ፓርቲ አጨዎች እንዲያዘነብሉ አድርጓቸዋል። የገዥው ፓርቲ የበላይነት ሕዝብ ያልመከረበትን የሕገመንግስት ለውጥ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ፈጠረ። የጥበቃ ኃይሎች የተቃውሞ አስተያየት ሰጪዎችንና የተቀዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችን እያፈሱ በማረፊያ ቤት አጉሩ፣ ደበደቡ። የእርሻ ሥራ ተስተጓጐለ፣ የግለሰቦችን ሀብት መንጠቁም ቀጠለ። ለብዙ ጊዜ ከተያዘ መሬት የማስነሳት ዘመቻ በ2005 ተካሂዶ 700,000 የሚሆን ሕዝብ መጠለያ አልባ ሆነ። አሁንም ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ እየተካሄደ ነው። ርዳታ ሊሰጡ የፈለጉ ሰብአዊ ድርጅቶች ተከለከሉ።

በታህሳሥ ሙጋቤና ታማኞቻቸው የፕሬዝዳንታዊው ምርጫ ለሁለት ዓመት እንዲዘገይ በማድረግ ወደ 2010 እንዲሸጋገር ሃሣብ አቀረቡ።

ፕሬዚደንት ፊደል ካስትሮ በመታመማቸው ለጊዜው በታናሽ ወንድማቸው በራውል ካስትሮ የሚመራውም የኩባ መንግስት ማናቸውንም የዜጐች መብቶች መጣሱን ቀጥሎበታል፡፡ በሰላማዊ መንገድ መንግስትን የመለወጥ መሠረታዊ መብት ወይም አብዮቱንም ሆነ መሪዎችን መተቸት ክልክል ነው፡፡

በ2006 መንግስት ተቃዋሚዎችን መውጫ መግቢያ ማሳጣቱን አጠናክሮ ቀጥሎበታል፡፡ ለመንግስት ደህንነት አደገኛ ናቸው ያላቸውን ሌሎች ዜጐችን እንዲሁ ቁም ስቅላቸውን እያሣየ ነው፡፡ ይህ የወከባ ተግባር "የማግለል ድርጊት" በሚባልና በቅስቀሳ በተነሣሱ በርካታ ሰዎች የሚካሄድ ሲሆን ድርጊቱ ማዋረድንና ድብደባን ይጨምራል፡፡ እስረኞችን የማዋረድና የመደብደብ ተግባር ማናላብኝነት የተፀናወተው ነው ::

ምንም እንኳን እዚህ ግባ የማይባል ቁጥር ያላቸው እስረኞች ባመቱ ውስጥ ቢለቀቁም በጥቂቱ 283 የሚሆኑ የፖለቲካ እስረኞች ዓመቱን በሙሉ በእስር ቤት ከርመዋል ::

ከዚህም መካከል በ2003 ዓ.ም. ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ተደርጎ በነበረው ተቃውሞ መንግሥት ካሠራቸው 75 ሰዎች ዛሬም 59ኙ በወህኒ ቤት ይገኛሉ ::

በ2006 *ቻይና* የሠብአዊ መብት ሬኮርድ ባንዳንድ አካባቢዎች ቁልቁል ወርዶ ታይቷል፡፡ ቁጥራቸው ያደገ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከፍ ባሉ ደረጃዎች ተከስተዋል፡፡ ከጥሰቶቹ ውስጥ ጥብቅ ክትትል፣ ማዋከብ፣ እንቅስቃሴን መግታትና ማሰር ይገኙበታል፡፡ የነዚህ ችግሮች ሰለባ የሆኑት የፖለቲካ ሰዎች፣ የሃይማኖት አራማጆች፣ ጋዜጠኞች፣ ደራሲያንና በሕግ በተፈቀደው መብታቸው መሠረት አገልግሎታቸውን ለደራበኞቻቸው ለማበርከት የሚፈልጉ ተከላካይ ጠበቆች ናቸው፡፡ የነዚህ ሰዎች ቤተሰቦች አንዳንድ አባላት ጭምር ተዋክበዋል። በእስር እንዲቆዩም ተደርገዋል፡፡ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሕዝባዊ ሰልፎችና። ለደረሱ ጉዳቶች ካሣ የሚጠይቁ ተቃውሞዎች በጭካኔ ተደምስሰዋል፡፡ አዳዲስ የመንግስት የቁጥጥር ስልቶች መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በድረገጽ መገናኛ፣ በፍርድ ቤቶችና በዳኞች ላይ ከሥራ ላይ ውለዋል፡፡ መዝገብ የማያውቃቸው የሃይማኖት ቡድኖችና አናሣ ብሔረሰቦች እንዳይንቀሳቀሱ ተደርገዋል :: በተለይ ደግሞ የኢይገርስና የቲቤታውያን ጉዳይ አሳሳቢ ነው ::

በቤላሩስ የሉካሸንኮ መንግስት የአፈና አገዛዙን አጠናክሮ ቀጥሎበታል፡፡ የመጋቢቱ ኘሬዜዳንታዊ ምርጫ በርካታ እንከኖች ነበሩበት፡፡ የምርጫውን ውጤት ባለመቀበል ለተቃውሞ ከወጡ ሰልፈኞች 1000 ያህል ታስረዋል፡፡ በርካቶችም ላጫጭር ጊዜ በሥር እንዲቆዩ ተደርጓል፡፡ በርካታ ተሳታፊዎችና የተቀዋሚ አባላት ሉካሸንኮን በኘሬዚዳንታዊ ምርጫ ለማሸነፍ የተወዳደሩት አሌክሳንደር ኮዙሊንን ጨምሮ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ተኩል ለሚደርስ ጊዜ እንዲታሰሩ ተደርጓል ::

የኤርትራ መንግስት ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች እጅግ በጣም የከፋ የሰብአዊ መብቶች ረገጣ የሚያካሂድ መንግስት መሆኑን አሁንም እንደቀጠለ ነው :: የሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ሬከርዱ በ2006 የባሰ እየተበላሸ ሄዶ የመንግስት ደህንነት ሃይሎች ያለፍርድ ግድያዎችን ፈጽመዋል፡፡ ወደ *ኢትዮጵያ* ለማምለጥ ወሰን ሲያቋርጡ የተገኙ ግለሰቦች በጥበቃ ኃይሎች መገደላቸውን ከሚታመኑ ዘገባዎች ለመረዳት ተችሏል :: መንግስት ብሔራዊ ዘመቻ ለማምለጥ የሚሞክሩ ወጣቶችን ይዞ የማሰር ዘመቻውን በከፍተኛ ደረጃ ከማሣደጉም

በላይ ቤተሰቦቻቸውን ጭምር እየያዘ ማሰሩን ተያይዞታል። የታሰሩ ሰዎች በእስር ቤት የማሰቃየት ተግባር እንደሚፈፀምባቸው የሚያመለክቱ የሚታመኑ ዘገባዎች ወጥተዋል ።

በ2005 እንደተደረገው ሁሉ መንግስት በርካታ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ሰብአዊ ድርጅቶችን ከሃገር እንዲወጡ አድርጓል። ምንም እንኳን በአፍሪካ ቀንድ የከፋ ድርቅ ቢኖርም ያላቋረጠ የሃይማኖት ገደቦች እየተደረጉ ነበር ።

በመላው ዓለም ግፊት እየተደረገበት የሚገኘው አራተኛው አሣዛቢ ሁኔታ የተጠናከረ በግለሰብ ደረጃ የፖለቲካ ተሳትፎ የማድረግ ነፃነት ነው። ይህ የተሳትፎ ነፃነት የፖለቲካና የማኅበረሰብ ለውጥ በሚያሰፈራቸው ወገኖች እያደገ የሚሄድ ተቃውሞ እየገጠመው ነው ።

የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለአንድ ሃገር ስኬት አስፈላጊ ናቸው ። ባለንበት ዓለም አገራትን የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ውስብስብ ናቸው ። የሲቪል ማኅበረሰብ አስተዋጽዖችና በነፃ የሚደረጉ የሃሳብ መንሸራሸሮች እንዲሁም የመረጃ ፍሰት ለሃገር ውስጥና ለዓለም አቀፍ ችግሮች መፍትሔ ፍለጋ በጅጉ አስፈላጊ ናቸው ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ከፖለቲካ ተሳታፊነት ማግለልና ነፃ የሆነ ሕዝባዊ ክርክርን እንዳይደረግ መከልከል ያንድን ማኅበረሰብ እድገት ያቀጭጫል ።

በያንዳንዱ የዓለም ክፍል በ2006 ለራስና ለፖለቲካ ነፃነት ለተነሱ ጥያቄዎች መንግስታት ምላሽ ሰጥተዋል። ምላሻቸው ግን ግዴታቸውን ለመወጣት ብለው ሣይሆን• ለሰብአዊ መብት ጥበቅና የቆሙና የሕዝብን ክብር የደፈሩ ተግባራትን ባጋለጡ እንደ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ነፃ የመገናኛ ብዙሃን ላይ-ድረገጽን ጨምሮ ጫና ለማሣደር ነው ። የሚያስደነግጥ ቁጥር ያላቸው ሃገሮች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የጋዜጠኞችን እንቅስቃሴዎች የሚያግዱ ሕግጋት አፀደቁ። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ጋዜጠኞች ሕገወጥ ለሆኑ ርምጃዎች ተጋልጠዋል ። ርምጃዎቹን የሚወስዱት ደግሞ የሚታወቁ ሰዎች አይደሉም ።

ለምሣሌ በ2006 በሩሲያ ውስጥ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከተ አዲስ ሕግ በጥር ወር ሥራ ላይ ውሏል ። ይህ ሕግ ጠበቅ ያሉ የምዝገባ ግዴታዎች፣ ጠንከር ያለ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት፣ ሰፊና አስቸጋሪ የሆኑ የሥራ ፕሮግራሞችንና ቀጥተኛ የሆኑ ሥራዎችን በግልጽ የማስቀመጥ ግዴታ መጣልና የፊዴራል ምዝገባ አገልግሎት ሰጪ ድርጅትም ምዝገባ የመፍቀድ ወይም የመከልከል አለዚያም የመዘጋት ሥልጣን የሰጠ ሕግ ነበር ። ሃሣብን በጽሁፍና በብዙሃን መገናኛ የመግለጽ ነፃነት በመንግስት ተፅእኖና በልዩ ልዩ ገደቦች የተነሣ በጅጉ አዘቅዝቋል ። በጥቅምት ወር የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪዋ የአና ፖሊትኮቭስካያ ሕይወት ባልታወቁ ነፍስ ገዳዮች አልፏል። እኒህ ጋዜጠኛ ሴት በቾችንያ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ረገጣ አስመልክቶ በሚጽፏቸው ገበና ገላጭ ጽሁፎች የታወቁ ነበሩ። መንግስት የብሔራዊ ቴሌቪዥኖችንና የሬድዮ ሥርጭቶችን በንቃት ይከታተላል። ተደማጭነት ያላቸውን የግዛት ጣቢያዎችንም እንዲሁ ይቆጣጠራል ። ጣጣ ያመጣሉ ብሎ የገመታቸውን መረጃ ሥርጭቶችን በሕዝብ ጆሮ እንዳይደርሱ ለማድረግ ሲል የሚያከናወነው ሥራ ነው ።

በቤላሩስ አስቸጋሪ የታክስ ቁጥጥርና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ላይ የተጣለው የምዝገባ ግዴታ የሲቭል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴ አስቸጋሪ አድርጐታል። በነፃው መገናኛ ብዙሃን ላይ የሚካሄደው

የጥቃት ዘመቻም በሰራተኞቹ ላይ እንዲሁ ችግር ፈጥሯል ። በጎዳር ወር የዴሞክራሲ ሥርዓት ቀንደኛው አራማጅ ዲሚትሪ ዳሽኬቪች ያልተመዘገበና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሥራን ሲመራ በመገኘቱ ለ18 ወራት በሥር እንዲቆይ ወህኒ ወርዷል ።

የካዛክስታን መንግስት ትሩ አክ ዞል የተባለው ተቀዋሚ ፓርቲ ከተባባሪ ሊቀመናብርቱ አንዱ ከተገደለበት በኋላ የፖለቲካ ሥራ መሥራት የሚያስችለው ምዝገባ ተደርጉለታል። መጀመሪያ *ሣርስንቤዶሊ* ተገደለ፤ ከዚያም ከውጪ በሚገኝ የርዳታ ገንዘብ የሚንቀሳቀስ ወገናዊ ያልሆነ ነገር ግን የፖለቲካ ፓርቲ ሥልጠና ሥራ ማካሄድና መረጃ ማቀበል የፖለቲካ ፓርቲውን በገንዘብ የመርዳት ያህል መሆኑን የሚያስታውቅን ሰውም ሆነ ድርጅት ከሥራው ላልተወሰነ ጊዜ ለማገድ ሲባል የሕገመንግስቱ አንቀጽ 5 ተዛብቶ በሥራ እንዲተርጉም ተደረገ ።

በሐምሌ ወር ኘሬዚዳንት ናዛርባየቭ አሳሪ የሆነ የብዙሃን መገናኛ ማሻሻያ ሕግ በፊርማቸው አጸደቁ ። የአውሮፓው የፀጥታና ትብብር ድርጅት የመገናኛ ብዙሃን ተወካይ ይህን ማሻሻያ" ወደ ኋላ አንድ ርምጃ" ሲሉ ገልፀውታል ። መንግስት ገዳቢ የሆኑ የሥም ማጥፋት ሕጐችን ሰዎችን ለመቅጣት፣ በወንጀለኛነት ለመፈረጅና የመገናኛ ብዙሃን ቀዳዳዎችን በመድፈን ጋዜጠኞችንና ትችት ፀሐፊዎችን ላልተወሰነ ጊዜ ዕድል ለማሣጣት ሥራውን ተጠቅሞበታል ። በሚያዝያ ወር አንድ እንዳይሰራ የታገደ የመገናኛ ብዙሃን ሠራተኛ ከፉኛ ተደብድቧል ።

ሃሣብን መግለጽ በማጎበር የመደራጀትና የመሰብሰብ ነፃነት *በቱርክሜኔስታን* በጥብቅ የተገደቡ ናቸው ። መንግስትም ማንኛውንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል። የውጪ ሣተላይት፤ የቴሌቪዥን ኘሮግራም በመላው *ቱርክሜንስታን* ያለችግር ይሠራጫል ። ይሁን እንጅ መንግስት ያገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃንን ይቆጣጠራል ። ጋዜጠኞችም ልዩ ፈቃድ ከሌላቸው በስተቀር ከውጪ ዜጐች ጋር ግንኙነት ማድረግ አይችሉም ። የመንግስት ንብረት በሆነው *በቱርክሜን ቴሌኮም* አማካይነት በጣም ውሱን በሆነ መንገድ በኢንተርኔት መገናኛ መጠቀም ይቻላል። ከሴኘቴምበር 2002 ጀምሮ ለአዲስ ደንበኛ ምዝገባ ተከልክሏል ። በዋና ከተማው በነሐሴ ወር መንግስት *ኦፉልስፓፓር ሚራዶቫ* ፣ አናኩርባን አማንክሊቼቭና ሣፓርዱርዲ ሃጂየቭ የተባሉ ጋዜጠኞችን ይዞ መሣሪያ ይዘው ተገኝተዋል በሚል ወንጀል በዝግ በተካሄደ የፍርድ ሂደት ከሰድስት እስከ ሰባት ዓመት እስራት አስፈርዶባቸዋል ።

የአውሮፓው ነፃ ራዲዮ ወይም የነፃነት ራዲዮ ቃል አቀባይ የነበረው ግለሰብ ሲገደል ሚራዶቫ የተባለችው ጋዜጠኛም እንዴት እንደሆነ ለማወቅ በሚያስቸግር ሁኔታ እስር ቤት እንዳለች ሴብተምበር ወር ሞታለች ። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዘገባዎች እንደሚያስረዱት ጦር መሣሪያ መደበቅ አለመደበቃቸውን ለማውጣጣት ሲባል ይህችን ጋዜጠኛና ሌሎች ሁለት ጓደኞቿ እስር ቤት እንዳሉ ከፍተኛ ግርፋትና ድብዳባ ተፈጽሞባቸዋል ። ኖቬንበር 21 ኘሬዚዳንት ሳፓራሙራት ኒያዞቭ ሞቱ ።

የኡዝቤክስታን መንግስት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሲል ከ200 በላይ የሚሆኑ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ዘጋ። ሕጉን ጥሳችኋል የተባሉ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሣይቀሩ የተጠቀሰው ርምጃ ስለባ ሆነዋል ። የግል ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ዛሬም ቁም ስቅላቸውን እያዩ ነው ።

የሶሪያ መንግስት የመረጃ ስርጭትን ሥራዬ ብሎ እየተቆጣጠረ ነው ። በመንግስት ላይ ትችት መስንዘርና የሃይማኖትንና የሕዳጣን መብቶችን ጨምሮ የልዩነት ጉዳዮችን አንስቶ ውይይትና ክርክር ማድረግ ከልክሏል ። እነዚህን እገዳዎች የጣሱ ግለሰቦች ለእሥር ተዳርገዋል። ሲከፋም የግል አስተያየት ሰጥታችኋል ተብለው ድብዳባ ደርሶባቸዋል ። ለምሳሌ የየካቲቱ የአዬል ማህፉዝ እስራት የተከተለው ነቢዩ ሙሃመድን አስመልክቶ በወጡ ካርቱኖች ዙሪያ የሃይማኖት ውይይት እንዲደረግ ጥሪ በማድረጉ ነው።

መንግስት ይህን ሁሉ ተግባር ሲፈጽም መሠረት አድርጐ የሚነሳው በኘሬስና በሕትመት ሕጐቹ ፤ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የኢንተርኔት አጠቃቀም ለመገደብ ባወጣው የአሸባኪይ ጊዜ ሕግና በገደብ እንዲሰሩ በወጣው የብዙሃን መገናኛ ደንቦች ላይ ነው ። በሃገር ውስጥ ሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ ብዙ ወከባ ደርሷል ። ያልተቋረጠ ክትትልና ለአውደ ጥናቶችና ለሰብሳቢዎች ተሳትፎ ሲባል ከሃገር በመውጣት መብት ላይ ማዕቀብ ተጥሏል ።

በኢራን የኘሬስ ነፃነት እንደ ምንጊዜውም የለም እስከሚያሰኝ ድረስ ዛሬም ዝቅተኛ ነው።ይህ ለመሆኑ ማስረጃው መንግስት የግል ጋዜጦች እንዳይታተሙ ማድረጉ ነው ። *ሻርግና ኢራን* የኢንተርኔት የዜና ድረገፆች ለሕዝብ እንዳይደርሱ ከልክለዋል ። በዚህ ረገድ የኒውዮርክ ታይምስንና ቢ.ቢ.ሲ በፋርስ ቋንቋ የሚያሰራጫቸው ዜናዎች ጭምር ክልክል ናቸው ። ከዚህም በላይ ጋዜጠኞችንና የድረገጽ ዜና አሰራጮችን መንግስት አስሯል ። ጋዜጠኞች ካገር እንዳይወጡ ማገድን ባለ ሥልጣናት እንደ ዋነኛ መሣሪያ ይጠቀሙበታል ።

በቡሩንዲ ማስር በእስር ቤት ማቆየትና ጋዜጠኞችንና የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎችን ማስፈራራትና ማሸማቀቅ የመንግስት የተዘወተረ ተግባር ነው ። ከብዙ ግለሰቦች በተጨማሪ ግንባር ቀደም የሆነውን የፀረ-ሙስና አራማጅ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ኘሬዚዳንት ፖሊስ ይዞ ለበርካታ ወራት አሰረው ። የአንድ ክፍለ ሃገር ገዥ የሃገሪቱን መሪ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሊግ ኢትካን "የሰላም ጠላት" ሲል ፈረጀው ። ኖቬምበር ወር ደግሞ አንድ የመንግስት ባለሥልጣን ዓመታዊ ሪፖርት አላቀረባችሁም በሚል ሰበብ ተመዝግበው በመላው ቡሩንዲ እንዲሰሩ ተፈቀዶላቸው የነበሩ 32 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሃገር እንደሚባረሩ አስታወቁ።

በሩዋንዳም ሲቭል ማኅበረሰቡ እንዳሻው እንዲንቀሳቀስ የሚያበረታታ ሁኔታ አለ ለማለት አያስደፍርም ። አገር በቀልም ሆኑ ዓለም አቀፍ መንግታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በያመቱ እንዲመዘገቡና ስለሚሰሩት ሥራ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ግዴታ ተጥሎባቸዋል ። ባለሥልጣናት ድርጅቶች ለሚያከናውኗቸው አንዳንድ ኘሮጀክቶች የመንግስት ፈቃድ ማግኘት የግድ እንደሆነ መመሪያ አውጥተዋል ። ይህ ግዴታ የዓለምአቀፍ ርዳታ ለማግኘት የሚያስችል ፈቃድ ማግኘትን ይጨምራል ። ከዚህ በተጨማሪ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ ሥራቸውን ያቀላጥፋል የተባለ የሕብረት ማህበርን መቀላቀል ይጠበቅባቸዋል ።

የቬኑዙዌላ መንግስት ሲቪል ማህበረሰቡን የማዋከብና የማስፈራራት ተግባሩን ቀጥሎበታል ።

በተለይ ደግሞ የምርጫ ሂደቶችን ለመታዘብ የቆመው ሱሜት የተሰኘው መያድ /መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት/ መሪዎች በአድማና ከውጭ አገር ገንዘብ ተቀብሎ አገርን በመክዳት ወንጀል ተከስዋል። ክሱ ለጊዜው የተቋረጠ ቢሆንም አሁንም አደጋው በአናታቸው ላይ እንዳነበበ አለ። በዓመቱ መጨረሻ ጉዳዩን አስመልክቶ በብሔራዊ

ምክር ቤቱ የወጣ ረቂቅ ሕግ ለውይይት ቀርቧል ። ይህ ሕግ ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ ድርጅቶች በሚያገኙት የገንዘብ ርዳታ ላይ መንግስት የቅርብ ክትትል እንዲያደርግ ያስችለዋል።አያያዙም ድርጅቶቹ በሰብዓዊ መብት ጥበቃና ዴሞክራሲን በማጐልበት ረገድ እንዳይሣተፉ ገደብ እንዲያስቀምጥባቸው ዕድል ያገኛል። የወንጀለኛ መቅጫ ማሻሻያዎች የመንግስት ባለስልጣናትን መሣደብ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑን ስለሚደነግጉና በጋዜጠኞች ላይም ጥቃት እያደረሱ በመሆኑ ለሰፈነው ራስን በራስ ሴንሰር የማድረግ ተግባር መንፈስ አስተዋፅኦ አድርገዋል። መንግስት ነፃ ተቀዋሚ በሆኑ የዜና ምንጮች ላይ የሚያካሂደውን የማዋከብ ተግባር አጠናክሮ ቀጥሎበታል። በታህሣስ ወር ፕሬዚዳንት ሻቬዝ በሃገሪቷ ረጅም ዕድሜ ያለውን የንግድ ጣቢያ የሬድዮ ካራካስ ቴሌቪዥን የዜና ማሰራጨት ፈቃዱ አይታደስም ብለዋል። የዚህን ዜና ማስራጫ ባለንብረቶችን "የመንግስት ግልበጣ ሱሰኞች" እና ሕዝብ በመንግሥት ላይ እምነት እንዳያሳድር አባዜ ያለባቸው ሲሉ ዘልፈዋቸዋል።

በቻይና ሀገር በቀልም ሆኑ ዓለምአቀፍ መያዶች ተከታታይና እየጨመረ በመሄድ ክትትልና ማዕቀብ እየተቸገሩ ናቸው። በ2006 መጨረሻ ላይ ድንበር የለሽ ዘጋቢዎች 31 ጋዜጠኞችና 52 የኢተርኔት ፀሐፊዎች ወህኒ መውረዳቸውን ሪፖርት አድርገዋል።መንግስት ባንድ በኩል ኢንተርኔት መጠቀምን ያበረታታል። በሌላ በኩል ባጠቃቀሙ ላይ ክትትል ያደርጋል፣ ይዘቱን ይቆጣጠራል፣ የሚተላለፈውን መረጃ ይወስናል፣ በመጨረሻም ያወጣቸውን ሕጐች የሚጥሱትን ይቀጣል። መንግስት ይዘታቸው ያላቸውን የዌብሣይቶች ድረገፆች አነጋጋሪ ናቸው ለተጠቃሚ እንዳይደርሱ አድርጓል። እንደሚባለው ከሆነ ባለስልጣናቱ ድረገፆችን ሙሉ ለሙሉ ከመዝጋት የተለያዩ ይዘቶችን ለይቶ ለተጠቃሚዎች የሚያደርስ የተራቀቀ ቴክኖሎጂ በጥቅም ላይ እንዲውል አድርጓዋል።

ቬትናምም ኢንተርኔትን ትቆጣጠራለች። አለምአቀፍ የሆኑ የሰብአዊ መብት የዜና ድረገፆች ታግዳለች። ዜጐች ብቃት በሌለው መንግስታዊ አስተዳደርና የሙስና መስፋፋትን በተመለከተ አቤቱታ እንዲያሰሙ የሀገሩ ሕግ ይፈቅዳል። ነገር ግን መንግስት የኮሚዩኒስት ፓርቲውን ሚና፣ የምድብ ለ ፓርቲ ዴሞክራሲን ወይም ደግሞ የሰብአዊ መብት ፖሊሲውን የሚጋፉ መጣጥፎች እትም እንዲያወጣ ኘሬሱን ከልክሏል። መንግስት በነፃ የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪዎች በኩል በቀጥታ የመረጃ ማግኘት ዕድልን ዘግቷል። የመረጃ ማዕከል ካፌ ባለቤቶች ደንበኞቻቸው የሚያስተላልፏቸውን መረጃዎችና የከፈቷቸውን ድረገጾች የመመዝገብ ግዴታ ጥለውባቸዋል ። መንግስት ዶ/ር ፋም ሆንግ ሳንን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ የሚታዩ የፖለቲካና የሃይማኖት ተቃዋሚዎችን ከእስር ፈትቷል። ዶ/ር ሳን በዴሞክራሲ ላይ የተፃፉ መጣጥፎችን ተርጉመው በድረገጽ አሰራጭተዋል ተብለው ታስረው ነበር። የዘር ማጥፋት ወንጀል ከሁሉም ጥፋት ይበልጥ ዘግናኙ ዕውነታ ነበር።

የተባበሩት መንግስታት አለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ድንጋጌ (ይህ ሰነድ የእስራኤላውያንን በናዚ ጀርመን መጨፍጨፍና በሁለተኛው የዓለም ጦሮች የታዩት አሰቃቂ ድርጊቶች የሰውን ልጅ ህሊና ምን ያህል እንዳቆሰለው የሚገልፅ ነው መግለጫ የነበረ ዶኪዩመንት) ከወጣ ከ60 ዓመታት በኋላ *በሱዳን የዳርፉር* ግዛት የዘር ማጥፋት ተግባር ዛሬም ቀጥሏል።

ጃንዋሪ 2005 በተደረገው ሁሉን አቀፍ የሰላም ስምምነት በሰሜንና በደቡብ ሱዳን መካከል የነበረው የ22 ዓመታት ጦርነት ቆሞ፣ ያንድነት መንግስት ቢፈጠርም፣ በሱዳን የጐሣ ግጭት ቀጥሏል። ይበልጥ ደግሞ መዓት የወረደ ያህል ግጭቱ በዳርፉር የከፋ ነው። በዳርፉር ለደረሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል መንግስትና

የመንግስት ድጋፍ ያላቸው የጃንጃዊድ ሚሊሺዎች ተጠያቂዎች ናቸው። የጥፋቱ ተሳታፊ የሆኑት ወገኖች ሁሉ የጭካኔ ወይም የብልግና ተግባር ፈጽመዋል። እኒህ ተግባራት የጅምላ ግድያን፣ ሴቶችን አስገድዶ መድፈርን እንደ ጦርነት ስልት መጠቀም፣ በስልት የሚፈፀም የማሰቃየት ተግባር፣ ዝርፊያና ህፃናትን ለውትድርና መመልመልን ያጠቃልላሉ። በ2006 መጨረሻ የዳርፉር ግጭት በትንሹ የ200,000 ሰዎችን ሞትና የሁለት ሚሊዮኖችን መፈናቀል አስከትሏል። 234,000 ሰዎች ወደ ጎረቤት ቻድ ተሰደዋል። ቻድና የማዕከላዊ አፍሪካ ሬፖብሊክ መንግስታት ከሱዳን ጋር በሚዋሰኑባቸው አካባቢዎች በጦሣ ግጭት ተቸግረዋል።

የአዲስ አበባውን ግጭት ማሳገጃ መንገድ ተቀብሎት የነበረ ቢሆንም የሱዳን መንግስት ዓለም አቀፍ ፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች በዳርፉር እንዲሰፍሩ ባለመፍቀድ በ2006 ሁለተኛው አጋማሽ ወታደራዊ ጥቃቱን ባዲስ ጉሰበት ቀጥሎበታል የፀጥታው ሁኔታ እየተበላሸ መሄዱ መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች የርዳታ መስጠት ሥራቸውን እንዲያቀዘቅዙ ወይም ደግሞ ጨርሰው እንዲያቆሙ አስገድዷቸዋል።

በሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ጋር አበሩ

የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ድንጋጌ ተስፋ ዕውን ይሆን ዘንድ የአለም አቀፍ ህብረተሰብ በተለይም የዓለም ዲሞክራሲ አራማጅ ዛሬ የሚታዩትን አሣሣቢ ሁኔታዎች ለውጥ የማይነካቸው አድርገው መቀበል አይችሉም። እርግጥ ነው እነዚህ ሰላም ነሺ ጉዳዮች ለሰው ልጅ ክብርና ለፖለቲካ ሁኔታ መሻሻል ከሚሰሩ ወገኖች ጋር ባንድ እንድንቆም ያስገድዱናል።

በ2006 የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች አበረታች ጥረቶች በዲሞክራሲያዊ መንግስታት ደምቀው እንዲታዩ ተደርጓል።

በ2006 የተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ በየሃገራቱ ላይ ክርክር ተደርጎ የተደረሰበት ሃሳብ በኢራን፣ በቤላሩስ፣ በሰሜን ኮሪያና በበርማ ለሚንቀሣቀሱ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች አስፈላጊው ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ አጽንዖት የሰጡ ውሳኔዎች አስተላልፏል።

በ2004 በኘሬዚዳንት ቡሽ ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ በ2005 ተቀባይነት ያገኘው የተባበሩት መንግስታት ዲሞክራሲ ፈንድ ባጥጋቢ ሁኔታ በሥራ ሲተገበር እነሆ አንድ ዓመት ሞላው አፈፃፀሙን በበላይነት እንዲመራ የተሠየመው ቦርድ ከ100 ሀገሮች በላይ ከቀረቡለት 300 ኘሮፖዛሎች ለ125ቱ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ተስማምቷል ይህ ባብዛኛው አፍቃሬ ዲሞክራሲ ለሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተፈቀደው ፈንድ ከ35 ሚሊዮን ዮስ ዶላር በላይ ነው።

በአካባቢ ደረጃ በ2006 የአሜሪካን መንግስታት ድርጅት (አ.መ.ድ.) ጠቅላላ ጉባኤ የአካባቢው አገሮች በጋራ ቃል የገቡበትንና ፈር ቀዳጅ የሆንውን የሳንቶ ዶሚንጐን ድንጋጌ ተቀበለዋል። ይህ ስምምነትም "የያንዳንዱን ሰው ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነትን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ይህም ኢንተርኔትን ጨምሮ በሁሉም የመገናኛ ብዙሀን ለሁሉም ሰው ክፍት እንዲሆን ነው። ያልተቀነጫጨበ የፖለቲካ ክርክር ። የየሀገሮቹ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች እነዚህን ተግባራት በሥራ እንዲተረጉሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ለመቀየስና በየጊዜውም እንዲሻሻሉ ለማድረግ ቁርጠኝነታቸውን አስታውቀዋል።

የአህጉርራዊ ድርጅት (OAS) ንዑስ ክፍል የሆነው የአሜሪካን ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፡ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በየሃገራቱ ስለሚያጋጥሟቸው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ችግሮች አንድ ሪፖርት አውጥቷል። ሪፖርቱ የእነዚህን ተሟጋቾች ሥራ መንግስታት ማገዝ እንዳለባቸው በአጽንኦት ይገልፃል።

ከሐምሌው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ቀደም ብሎ 19 የሚሆኑ አፍሪካውያን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በጋምቢያ ዋና ከተማ ባንጁል ውስጥ ተሰብስበው ነበር። የነዚህ ድርጅቶች ስብሰባ ዋነኛ ዓላማ ሀገራት የስምምነት ግዴታዎችን እንዲያከብሩ በአፍሪካዊ የአቻ ግምገማ ዘዴ ላይ የሲቪል ማህበረሰባት ስለሚኖራቸው ሚና ለመሪዎቹ ጉባዔ ሃሣብ ለማቅረብ ነበር። በሌላም በኩል የሲቪል ማህበረሰባቱ መረጃዎችን እንዴት ይፋ ማድረግ እንዳለባቸውና መድሎን የሚያስቀሩ የዜግነት ሕጐችን መደንገግ እንዴት እንደሚቻል ጭምር ለመሪዎቹ ሃሣብ ማቅረብን ያካትታል። በመጨረሻም እነዚህ ሃሣቦች ለመሪዎቹ ጉባዔ ቀርበው ተቀባይነት አግኝተዋል።

ስፋት ባለው የመካከለኛው ምሥራቅና የሰሜን አፍሪካው ክልል ያሉ ሀገሮች ዮርዳኖስ ውስጥ በሚገኘው ሙት ባሕር ውስጥ በተደረገ በመጪው ጊዜ ላይ ለመምከር ስብሰባ አደረጉ። የክልሉን የመንግስት ባለሥልጣናትና የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች ከቡድን 8 አጋር አገራት ጋር አገናኘ። ወደ 50 የሚጠጉና በ16 አገሮች ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ድርጅቶች የሚወክሉ የሲቪል ማህበረሰብ መሪዎች ስለ ሕግ የበላይነት፣ ስለ አሠራር ግልጽነት፣ ሴቶችንና ሕፃናትን ስለ መብታቸው እንዲያውቁና በህብረተሰባቸው ውስጥ ተገቢውን ስፍራ እንዲይዙ ስለማድረግ እንዲሁም ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስለሚኖራቸው ሕጋዊ የሥራ ክልል በተደረጉ ውይይቶች ላይ ተካፍለዋል። ውሣኔ በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ክትትል ለማድረግ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ስለመቀየስና ማሻሻያዎችን ስለማጠናከር ውይይት አድርገዋል። ይሁን እንጅ አስቸጋሪውና እልህ አስጨራሹ ጉዳይ በሲቪል ማህበረሰባቱ የቀረቡ ሐሣቦችን ተቀብሎ በሥራ የመተርጐመ ነገር ነው። ስብሰባው ያስገኘው ትልቁ ነገር ከዚህ በፊት በክልሉ ያልነበረ ሲቪል ማህበረሰባት ከመንግስት ጋር ተቀራርበው ለመሥራት የሚያስችል የፖለቲካ ሥፍራ እንዲኖራቸው ማስቻሉ ነው።

ዲሴንበር 2006 የተከበረውን የአለምአቀፍ ሰብአዊ መብት ቀንን ምክንያት በማድረግ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯ ራይስ የሰብአዊ መብትና ዴሞክራሲ አቀንቃኞችን መደገፍ የሚያስችሉና በጣም ጠቃሚ የሆኑ የእርምት ሀሳቦችን አቀረቡ። ሚኒስትሯ "የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ፈንድ" የተባለ የገንዘብ ምንጭ መፈጠሩን አበሠሩ። ይህ ፈንድ የመንግስት ጭቆና ለሚገጥማቸው ተሟጋቾች አንዳንድ ሥራዎቻቸውን የሚያቀላጥፉባቸው ከውጪ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሚሰጡ አነስተኛ ወጪዎችን የሚያካትት ነው። ይህ ፈንድ ለሕጋዊ የፍርድ ቤት ጉዳዮች፡ የሕክምና ወጪዎች ወይም ደግሞ ለተሟጋች ቤተሰቦች አጣዳፊ የገንዘብ ችግሮች የሚውል ነው።

የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ራይስ፡ መንግስታት መያዶችን ስለሚይዙበት ሁኔታ አሥር መርሆዎችን አውጥተዋል። እነዚህ ዓይነተኛ መርሆዎች የአሜሪካ መንግስት መያዶችን ስለሚያስተናግድበት ሁኔታ በግልጽ አስቀምጠዋል። የሌሎች መንግስታትን አሠራሮችም እንገመግምባቸዋለን ብለዋል። መርሆቹ ረጃጅምና ዝርዝር የሆኑ የተባበሩት መንግስታትና ዓለምአቀፍ ሰነዶች ያሰፈሯቸውን መርሆች ለማገዝ የተቀረጹ ሲሆን በተቀሚዎች ለተከበቡ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች መያዶች ዓለምአቀፍ ድጋፍ እንዲያገኙ ታስቦ ነው። መርሆዎቹ ለመንግስት፣ ለዓለምአቀፍ ድርጅቶች፣ ለሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖችና ለጋዜጠኞች አመቺ መሣሪያዎች እንዲሆኗቸውም ታልሞ የተረቀቁ ናቸው።

የማህበራዊ እኩልነትና የውሳኔ ሰጪ ተሳታፊዎች ለሰብአዊ መብት ጠበቆችና ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ድጋፍ ሲያደርጉ በመላው ዓለም የሚኖሩ ሕዝቦች የራሣቸውን የወደፊት ዕጣ ፋንታ በነፃነት እንዲወስኑ እረዳናቸው ማለት ነው ብለዋል። እንዲህ በማድረጋችንም የሰው ዘር ለተባለ ሁሉ የተመቸና ሰላማዊ የሆነ ዓለም ለመፍጠር አግዘን ማለት ነው።

የሰላምና የዴሞክራሲ ለውጥ ሐዋርያት በመሆናቸው የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን አበክረን ጥብቅና ልንቆምላቸው ይገባል።